የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 41
ADDIS ABABA - 4th July, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፩/፲፱፻፺፪ ዓ.ም
የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ...ገጽ ፩ሺ፫፻፷፯

## CONTENTS

Proclamation No. 211/2000
Institution of the Ombudsman Establishment Proclamation ........................................Page 1367

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፩/፲፱፻፺፪
## የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት እንዲሁም ለሕግ ልዕልና እውነት ባካሄደው ረጅም ትግል የከፈለው መስዋዕትነት በዜጎች ላይ በዘፈቀደ የሚፈጸሙ የአስተዳደር በደሎች የሚቀጩበትን ወይም የሚታረሙበትን ቀልጣፋ አሠራር በመዘርጋት ለሰናይ መስተዳድር መሠረት የመጣልን ወቅታዊ እርምጃ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባሮች ከዜጎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ያላቸው ቁርኝትና ከመብታቸው ጋር በተሳሰረ ሁኔታ የሚኖራቸው የወሳኝነት ሥልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደገና እየሰፋ በመምጣቱ፤

በዚህ ሂደት የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው የሚሰጧቸውን ፍትሃዊነት የጎደላቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በወቅቱ ማረም ወይም እንዳይደርሱ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

አስተዳደራዊ ጥፋት የተፈጸመባቸው ዜጎች ተጎድተው እንዳ ይቀሩ በቀላሉ ቅሬታቸውን የሚያሰሙበትና መፍትሄ የሚሹበት ተቋም የማግኘት ፍላጎታቸው መሟላት ያለበት በመሆኑ፣

ሕግ አውጪው በሕዝብ ተወካይነቱ ሕግ አስፈጻሚው አካል ተግባሩን በሕግ መሠረት የሚያከናውንና የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የዜጎችን መብቶች የማይጋፉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO. 211/2000
## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE INSTITUTION OF THE OMBUDSMAN

WHEREAS, the immense sacrifice paid by the people of Ethiopia, in the protracted struggle they waged with a view to securing political power and to realizing the rule of law, calls for taking the due measure of laying the foundation for good governance, by way of setting up an easily accessible means for the prevention or rectification of administrative abuses arbitrarily committed against citizens;

WHEREAS, the interlinkage of the activities, and of the decision–making power, of executive organs of government with the daily lives and the rights of citizens is an ever–increasing and widening circumstance;

WHEREAS, it is necessary to duly rectify or prevent the unjust decisions and orders of executive organs and officials thereof, given under said circumstance;

WHEREAS, in order that citizens, having suffered from maladministration, are not left without redress, their want for an institution before which they may complain and seek remedies with easy access needs to be fulfilled;

WHEREAS, the legislature, as a representative of the people, has the responsibility to ensure that the executive organ carries out its functions in accordance with the law and that its administrative decisions are not rendered in violation of citizens' rights;

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

ያንዱ ዋጋ 4·85
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ይህንኑ መርህ ለማጎልበትና ስለሕግ አውጪው ሆኖ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ በመሆን ከሚያገለግሉት ተቋሞች መካከል አንዱ የሆነውን የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ማቋቋምና ሥልጣኑንና ተግባሩን በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፭) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፩/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩· "ተሿሚ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በምክር ቤቱ የሚሾም ዋና ዕንባ ጠባቂ፣ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ወይም በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ደረጃ የሚገኝ ወይም የህፃናትንና የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተል ዕንባ ጠባቂ ማለት ነው።

፪· "ሠራተኛ" ማለት የተቋሙ መምሪያ ኃላፊዎችን፣ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ይጨምራል፣

፫· "ቤተዘመድ" ማለት በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ መሠረት የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው፣

፬· "ምክር ቤት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፣

፭· "የአስተዳደር ጥፋት" ማለት ማናቸውንም የአስተዳደር ሕግን ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግን ወይም ሌሎች አስተዳደር ነክ ሕጎችን በመፃረር በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ወይም የሚሰጡ ውሳኔዎችን ይጨምራል፣

፮· "ባለሥልጣን" ማለት የሕዝብ ተመራጭ ወይም የመንግሥት አስፈጻሚ አካል ተሿሚ ወይም ኃላፊ ነው፣

፯· "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

፰· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) ላይ የተመለከቱት ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፣

፱· "መንግሥት" ማለት የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት ነው፣

፲· "የመንግሥት የልማት ድርጅት" ማለት በመንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኝ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ አገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ ዓይነት ድርጅት ነው፣

፲፩· "የመንግሥት መ/ቤት" ማለት ሚኒስቴር፣ ኮሚሽን፣ ባለሥልጣን፣ ኤጀንሲ፣ ኢንስቲትዩት ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፣

፲፪· "መርማሪ" ማለት የምርመራ ሥራ እንዲያካሂድ በዋና ዕንባ ጠባቂው የተመደበ ሠራተኛ ነው ፣

፲፫· "አስፈጻሚ አካል" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤትን፣ ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንዲሁም በዳኝነት ሰጭ ወይም በሕግ አውጪው አካል ውስጥ የአስተዳደር ወይም የአስተዳደር ነክ አገልግሎት የሚሰጥ አካልን ይጨምራል፣

፲፬· "ሕግ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን፣ የክልል ሕገ መንግሥትን፣ የፌዴራል ወይም የክልል ሕጎችንና ደንቦችን ይጨምራል።

WHEREAS, with a view to enhancing the principle thereof, it is found necessary to establish, and to determine the powers and duties of, the Office of Ombudsman, as one of the parliamentary institutions instrumental in the control of the occurrence of maladministration;

NOW, THEREFORE, in accordance with of Article 55 (1) and (15) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## *General Provisions*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Institution of the Ombudsman Establishment Proclamation No. 211/2000."

2. *Definitions*

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1) "Appointee" means the Chief Ombudsman, the Deputy Chief Ombudsman or an Ombudsman, at the level of a branch office or who follows up the affairs of children and women appointed in accordance with this Proclamation;
2) "Staff" includes department heads, professionals and the support staff of the Institution;
3) "Family Member" means a person of relation by consanguinity or affinity, in accordance with the Civil Code of Ethiopia;
4) "House" means the House of Peoples' representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
5) "Maladministration" includes acts committed, or decisions given, by executive government organs, in contravention of administrative laws, the labour law or other laws relating to administration;
6) "Official" means an elected representative or an appointee or official of an executive government organ;
7) "Person" means any natural or juridical person;
8) "Region" means any of those specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the pruposes of this Proclamation, includes the Addis Ababa City Administration and the Dire Dawa Administration;
9) "Government" means the Federal, or a Regional Government;
10) "Public Enterprise" means a production, distribution, service rendering or other enterprise, under the ownership of the Federal or a Regional Government;
11) "Government Office" means a Ministry, a Commission, an Authority, an Agency, an Institute or any other government office;
12) "Investigator" means a staff assigned, by the Chief Ombudsman, to conduct an investigation;
13) "Executive Organ" includes a government office or a public enterprise as well as organs rendering administrative or related services within the judiciary or the legislature;
14) "Law" includes the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the Constitution of a Region as well as federal or regional laws and regulations.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

፫· መቋቋም

፩· የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም (ከዚህ በኋላ "ተቋሙ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ተቋሙ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል።

፬· የተፈጻሚነት ወሰን

፩· በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

፪· ይህ አዋጅ በክልል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው በሚፈጸሙ የአስተዳደር ጥፋቶችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፭· ዓላማ

የተቋሙ ዓላማ በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈጻሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ፣ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ይሆናል።

፮· ሥልጣንና ተግባር

ተቋሙ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩· አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች ፣ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና አሠራሮቻቸው የዜጎችን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችንና ሕጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር፣

፪· አስተዳደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመቀበልና የመመርመር፣

፫· አስፈጻሚው አካል ሥራውን በሕግ መሠረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ፣

፬· አስተዳደራዊ ጥፋት መፈፀሙን ያመነበት ከሆነ የመፍትሄ ሃሳብ የመሻት፣

፭· አስተዳደራዊ ጥፋቶች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የማጥናትና ሃሳብ የማቅረብ፣

፮· የተሻለ የመንግሥት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ሕጎች ወይም አሠራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ፣

፯· ከዓላማው ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን።

፯· የሥልጣን ገደብ

ተቋሙ፦

፩· በሕዝብ ምርጫ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች በሕግ አውጭነታቸው የሚሰጧቸው ውሳኔዎችን ወይም፣

፪· በማንኛውም ፍርድ ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን ወይም፣

፫· በዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን ወይም፣

፬· በፀጥታ ኃይሎችና በመከላከያ ሠራዊት ክፍሎች የሚሰጡ የፀጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሳኔዎችን፣

የመመርመር ሥልጣን የለውም።

፰· የተቋሙ አቋም

ተቋሙ፦

፩· የዕንባ ጠባቂ ጉባዔ፣

፪· ሀ) አንድ ዋና ዕንባ ጠባቂ፣

ለ) አንድ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ፣

ሐ) የሕፃናትና የሴቶችን ጉዳይ የሚመራ ዕንባ ጠባቂ፣

መ) የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዕንባ ጠባቂዎች፣ እና

ሠ) አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች

ይኖሩታል።

፱· ዋና መሥሪያ ቤት

የተቋሙ ዋና መ/ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ምክር ቤቱ በሚወስነው በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል።

3. *Establishment*

1) The Institution of the Ombudsman (hereinafter referred to as "the Institution") is hereby established as an autonomous organ of the Federal Government having its own juridical personality.
2) The Institution shall be accountable to the House.

4. *Scope*

1) The Provisions of this Proclamation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.
2) This Proclamation shall also apply to maladministration committed by the executive organs, and officials thereof, of a Regional Government.

5. *Objective*

The objective of the Institution shall be to see to bringing about good governance that is of high quality, efficient and transparent, and are based on the rule of law, by way of ensuring that citizens' rights and benefits provided for by law are respected by organs of the executive.

6. *Powers and Duties*

The Institution shall have the powers and duties to:

1) supervise that administrative directives issued, and decisions given, by executive organs and the practices thereof do not contravene the constitutional rights of citizens and the law as well;
2) receive and investigate complaints in respect of maladministration;
3) conduct supervision, with a view to ensuring that the executive carries out its functions in accordance with the law and to preventing maladministration;
4) seek remedies in case where it believes that maladministration has occurred;
5) undertake studies and research on ways and means of curbing maladministration;
6) make recommendations for the revision of existing laws, practices or directives and for the enactment of new laws and formulation of policies, with a view to bringing about better governance;
7) perform such other functions as are related to its objective.

7. *Limitation of Power*

The Institution shall have no power to investigate:

1) decisions, given by Councils established by election, in their legislative capcity;
2) cases pending in courts of Law of any level;
3) matters under investigation by the Office of the Auditor-General; or
4) decisions given by Security Forces and units of the Defence Forces, in respect of matters of national security or defence.

8. *Organization of the Institution*

The Institution shall have:

1) a Council of the Ombudsman
2) (a) a Chief Ombudsman;
   (b) a Deputy Chief Ombudsman;
   (c) an Ombudsman heading the children and women affairs;
   (d) Ombudsmen heading branch offices; and
   (e) the necessary staff.

9. *Head Office*

The Institution shall have its Head Office in Addis Ababa and it may have branch offices in other places to be determined by the House.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

፲· <u>አሿሿም</u>

፩· ዋና ዕንባ ጠባቂ፡ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂና ሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች በምክር ቤቱ ይሾማሉ።

፪· የዋና ዕንባ ጠባቂ፡ የምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂና የሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች አሿሿም የሚከተለው የአመራረጥ ሥርዓት ይኖረዋል፡

ሀ) ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ መሠረት በሚቋቋመው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ይመለመላሉ፡

ለ) ዕጩዎቹም በኮሚቴው ሁለት ሦስተኛ ድምፅ የተደገፉ መሆን አለባቸው፡

ሐ) ዕጩዎቹ በምክር ቤቱ አፈ–ጉባዔ ለምክር ቤቱ ቀርበው ድምጽ የሚሰጥባቸው ይሆናል፤

መ) የቀረቡት ዕጩዎች በምክር ቤቱ ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲደገፉ ይሾማሉ።

፲፩· <u>የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ጥንቅር</u>

የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩· የምክር ቤቱ አፈጉባዔ.............................. ሰብሳቢ፤

፪· የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ .................... አባል፤

፫· ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ አምስት አባላት ............................................ ” ፤

፬· በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በጋራ ስምምነት የሚመረጡ ሁለት የምክር ቤቱ አባላት.......................... ” ፤

፭· የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት............................................... ” ፤

፲፪· <u>ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው በዕንባ ጠባቂነት ሊሾም ይችላል፡

፩· ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ተገዥ የሆነ፡

፪· በሕግ ወይም በአስተዳደር ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሙያ የሰለጠነ ወይም በልምድ በቂ ዕውቀት ያካበተ፤

፫· በታታሪነቱ፡ በታማኝነቱ እና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤

፬· ከደንብ መተላለፍ ውጪ ባለ በሌላ የወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፡

፭· ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፡

፮ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው፡ እና

፯ ዕድሜው ከ፴፭ ዓመት በላይ የሆነ።

፲፫· <u>ተጠሪነት</u>

፩· ዋና ዕንባ ጠባቂ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል።

፪· ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂውና ሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች ተጠሪነታቸው ለዋናው ዕንባ ጠባቂ ይሆናል።

፲፬· <u>የሥራ ዘመን</u>

፩· የማንኛውም ተሿሚ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው የሥራ ዘመን ካበቃ በኋላ ተሿሚው እንደገና ሊሾም ይችላል።

፫· በአንቀጽ ፲፭ (፩) መሠረት ሹመቱ ቀሪ የተደረገበት ወይም ከኃላፊነት የተነሳ ሰው እንደገና ካልተሾመ በስተቀር ለስድስት ወር ያህል በሕግ አውጪ፤ በሕግ አስፈጻሚ ወይም በዳኝነት አካላት ውስጥ የኃላፊነት ቦታ አይሰጠውም።

10. *Appointment*

1) The Chief Ombudsman, the Deputy Chief Ombudsman and other Ombudsmen shall be appointed by the House.

2) The appointment of the Chief Ombudsman, the Deputy Chief Ombudsman and of other Ombudsmen shall be made as under the following procedure:

(a) the appointees shall be recruited by a Nomination committee to be formed pursuant to Article 11 hereunder;

(b) the nominees shall have to receive the support of a two–thirds vote of the members of the Committee;

(c) the list of nominees shall be presented to the House, by the Speaker, to be voted upon;

(d) the nominees shall be appointed upon receipt of a two–thirds vote of the House.

11. *Composition of the Nomination Committee*

The Nomination Committee shall have the following members:

1) the Speaker of the House...................... Chairperson

2) the Speaker of the House of the Federation...............................................Member(s)

3) five members to be elected by the House from among members ........................... ,,

4) two members of the House to be elected by joint agreement of opposition parties having seats in the House ......................... ,,

5) the President of the Federal Supreme Court. .................................................. ,,

12. *Criteria for Appointment*

Any person who:

1) is loyal to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2) is trained in law, administration or other relevant discipline or has acquired adequate knowledge through experience;

3) is reputed for his diligence, honesty and good conduct;

4) has not been convicted for a criminal offence other than petty offence;

5) is Ethiopian National

6) is of enough good health to assume the post; and

7) is above thirty–five years of age;

may be appointed as an Ombudsman.

13. *Accountability*

1) The Chief Ombudsman shall be accountable to the House.

2) The Deputy Chief Ombudsman and other Ombudsmen shall be accountable to the Chief Ombudsman.

14. *Term of Office*

1) The term of office of an appointee shall be five years.

2) Upon expiry of the term of office specified under sub–Article (1) of this Article, an appointee may be re–appointed.

3) An appointee discharged from responsibility or removed from office, as under Article 15(1) hereunder, shall not, unless reappointed, assume a post in legislative, executive and judicial organs for about six months thereafter.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

፲፭· ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ምክንያት

፩· አንድ ተሿሚ በሚከተሉት ሁኔታዎች ከኃላፊነት እንዲነሳ ወይም ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል፡

ሀ) ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግና አስቀድሞ የሦስት ወር ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ሲሰጥ ፡ ወይም

ለ) በህመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ፡ ወይም

ሐ) በሙስና መሥራቱ ወይም ሕግን የሚጻረር ሌላ ድርጊት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ፡ ወይም

መ) ግልጽ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፡ ወይም

ሠ) የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ።

፪· አንድ ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከኃላፊነት ከተነሳበት ወይም ሹመቱ ቀሪ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወሮች ውስጥ በሌላ ተሿሚ መተካት ይኖርበታል።

፲፮· ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ሥነ ሥርዓት

፩· አንድ ተሿሚ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ (፩) ከ(ለ)–(መ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች መሠረት ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን የሚደረገው ጉዳዩ በአንቀጽ ፲፯ መሠረት በሚቋቋመው ልዩ አጣሪ ጉባዔ ከተመረመረ በኋላ ይሆናል።

፪· ምክር ቤቱ በልዩ አጣሪ ጉባዔው አብላጫ ድምጽ ተደግፎ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ሲያምንበትና በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲደግፈው ተሿሚው ከኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል።

፲፯· የልዩ አጣሪ ጉባዔው ጥንቅር

ልዩ አጣሪ ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

፩· የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ.................... ሰብሳቢ፣

፪· የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ.....................አባል፣

፫· ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ ሦስት አባላት..................................................አባል፣

፬· በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጋራ ስምምነት የሚመረጥ አንድ የም/ቤቱ አባል ........................................ " ፣

፭· የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ..................................................... " ።

፲፰· በሌላ ሥራ መሰማራት ስለመከልከሉ

፩· ተሿሚው በሥራ ዘመኑ ክፍያን በሚያስገኝ በሌላ የመንግሥትም ሆነ የግል ቅጥር ሥራ ላይ እንዲሠማራ አይፈቀድለትም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ተሿሚው አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚፈለግበት የተለየ የሙያ መስክ ከግምት ውስጥ ገብቶ በምክር ቤቱ ሊፈቀድለት ይችላል።

ምዕራፍ ሁለት

የተሿሚዎች ሥልጣንና ተግባሮች

፲፱· የዋና ዕንባ ጠባቂው ሥልጣንና ተግባር

፩· ዋናው ዕንባ ጠባቂ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ ለተቋሙ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዕንባ ጠባቂ፣

ሀ) የተቋሙ የዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡

ለ) የተቋሙን በጀት አዘጋጅቶ በቀጥታ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

ሐ) በቂ ምክንያት ሲኖረው አንድ ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ወደ ሌላ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ያዛውራል ፡ ወይም በማንኛውም ሥፍራ የተፈጸመ አስተዳደራዊ ጥፋትን በራሱ ይመረምራል፡

15. *Grounds for Removal of an Appointee*

1) An appointee may be removed from office or discharged from responsibility upon the following circumstances:

(a) upon resignation, subject to a three–month prior written notice;

(b) where it is ascertained that he is incapable of properly discharging his duties due to illness;

(c) where he is found to be corrupt or to have committed other unlawful act;

(d) where it is ascertained that he is of manifest incompetence;

(e) upon termination of his term of office.

2) Within six months of the removal or discharge of an appointee, as under Sub–Article (1) of this Article, another appointee shall be made to replace him.

16. *Procedure for Removal of an Appointee*

1) An appointee shall be removed from office, upon the grounds specified under Article 15 Sub Article (1) (b)-(d) herein, subsequent to investigation of the matter by a Special Inquiry Tribunal to be formed under Article 17 hereof.

2) An appointee shall be removed from office where the House finds that the recommendation submitted to it, as supported by the majority vote of the Special Inquiry Tribunal, is correct and where it upholds same by a two–thirds majoirty vote.

17. *Composition of the Special Inquiry Tribunal*

The special Inquiry Tribunal shall have the following members:

1) the Deputy Speaker of the House..........Chairperson

2) the Deputy speaker of the House of Federation .............................................Member(s)

3) three members to be elected by the House..... "

4) a member of the House to be elected by joint agreement of opposition parties having seats in the House.............................. "

5) the Vice–President of the Federal Supreme Court.......................................................... " .

18. *Prohibition to Engage in Other Employment*

1) An appointee shall not be allowed to engage in other gainful, public or private employment during his term of office.

2) Notwithstanding the provisions of Sub–Article (1) of this Article, the House may allow otherwise in consideration of the particular profession in which the appointee is required to make contribution.

PART TWO

*Powers And Duties Of Appointees*

19. *Powers and Duties of the Chief Ombudsman*

1) The Chief Ombudsman shall be the superior head of the Institution and, as such, shall exercise the powers and duties of the Institution provided for under this Proclamation.

2) Without prejudice to the generality stated under Sub–Article (1) of this Article, the Chief Ombudsman shall:

(a) employ and administer the staff, in accordance with the directive to be adopted by the Council of the Ombudsmen.

(b) prepare and directly submit, to the House, the budget of the Institution and implement same upon approval;

(c) transfer a case, where he has sufficient grounds, from one investigation section or investigator to another or to himself, or/and investigate a case of maladministration occurring anywhere;

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

መ) ተደጋጋሚ የአስተዳደር ጥፋቶችን አጥንቶ ከመፍትሄ ሃሳብ ጋር ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ሠ) አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ረቂቅ ሕጎችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ በሌሎች አካላት በተዘጋጁ ላይ አስተያየት ይሰጣል፣

ረ) አስተዳደራዊ ጥፋቶችንና የተቋሙን ሥራ አካሄድ አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሰ) ተቋሙን በመወከል በስብሰባዎች ይካፈላል፣ ከፌዴራሉና ከክልል መንግሥታት አካላት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣

ሸ) ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣

ቀ) በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፫· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ)፣ (ሠ)፣ (ረ) እና በአንቀጽ ፴፭ (፪) ከተጠቀሱት በስተቀር ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ዋና ዕንባ ጠባቂው ለተቋሙ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለዕንባ ጠባቂዎች ወይም ለሌሎች ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

፳· የምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ሥልጣንና ተግባር

ከዋና ዕንባ ጠባቂው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት፣

፩· የተቋሙን ዋና መሥሪያ ቤት ተግባራትን በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዕንባ ጠባቂውን ይረዳል።

፪· ዋና ዕንባ ጠባቂው በማይኖርበት ጊዜ ለዋናው ዕንባ ጠባቂ የተሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል።

፫· በዋናው ዕንባ ጠባቂ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፳፩· የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የዕንባ ጠባቂዎች ሥልጣንና ተግባር

ዕንባ ጠባቂው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፮ በተቋቋመበት ሥፍራ ውስጥ ለተቋሙ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

፩· የመንግሥት የአስተዳደር ሕጎች እና ሌሎች ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን የማረጋገጥ፣

፪· በቂ ምክንያት ሲኖር አንድ የአስተዳደር ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም ከአንድ መርማሪ ወደ ሌላ የማዛወር ወይም እራሱ ምርመራ የማካሄድ፣

፫· አስተዳደራዊ ጥፋቶችን በተመለከተ ለዋናው ዕንባ ጠባቂና በተቋቋመበት ሥፍራ ለሚገኝ ክልል መንግሥት ዝርዝር ሪፖርት የማቅረብ፣

፬· ከመልካም አስተዳደር መርህ ጋር የማይጣጣሙ ሕጎችና የአሠራር ልምዶች እንዲሻሻሉ ሃሳብ የማቅረብ፣

፭· በተቋሙ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የመምራት፣

፮· ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያዎችን የመፈጸም፣

፯· ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን በመወከል ከክልል መንግሥት አካላትና በተቋቋመበት ሥፍራ ውስጥ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት የማድረግ፣

፰· በዋና ዕንባ ጠባቂው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች የማከናወን።

## ምዕራፍ ሦስት
## የተቋሙ የአሠራር ደንቦች

፳፪· አቤቱታ የማቅረብ መብት

፩· አቤቱታ የሚቀርበው መብቴ ተጥሶብኛል በሚል ሰው፣ ወይም በሚስት ወይም በባል ወይም በቤተዘመድ ወይም በወኪል ወይም በሦስተኛ ወገን ሊሆን ይችላል።



(d) undertake study of recurrent cases of maladministration and forward together with remedial proposals to the House;

(e) prepare and submit draft administrative legislations, give his opinion on those prepared otherwise;

(f) submit a report, to the House, on matters of maladministration and on the activities of the Institution;

(g) take part in meetings by way of representing the Institution, establish working relations with Federal and Regional government organs as well as with non–governmental organizations;

(h) organize, as well as coordinate, and follow up the activities of branch offices;

(i) undertake such other activities as are assigned to him by the House.

3) The Chief Ombudsman may, to the extent necessary for the efficient performance of the Institution, delegate part of his powers and duties, other than those specified under Sub–Article (2)(b),(e) and (f) of this Article, and Article 35(2), to Ombudsmen or to other officials of the Institution.

20. *Powers and Duties of the Deputy Chief Ombudsman*

Pursuant to directives given from the Chief Ombudsman, the Deputy Chief Ombudsman shall:

1) assist the Chief Ombudsman in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the head office of the Institution;
2) undertake the activities of the Chief Ombudsman in the absence of the latter;
3) carry out such other activities as may be assinged to him by the Chief Ombudsman.

21. *Powers and Duties of Ombudsmen of Branch Offices*

In addition to exercising the powers and duties of the Institution specified under Article 6 of this Proclamation within the local jurisdiction of a branch office, an Ombudsman shall, as the superior head of a branch office, have the following powers and duties:

1) to ensure that administrative and other laws, regulations, and directives, are observed;
2) to transfer an administrative case from one investigation section or investigator to another or to conduct the investigation himself, where it has a good cause;
3) to submit, to the Chief Ombudsman and to the government of the Region wherein it is situate, a detailed report on matters of maladministration;
4) to forward proposals for the revision of laws and practices inconsistent with principles of good governance;
5) to direct the branch office, in accordance with directives given from the Institution;
6) to effect payments in accordance with the budget allocated to the branch office;
7) to establish working relations, as a representative of the branch office, with Regional government organs and non-governmental organizations operating within its local jurisdiction;
8) to perform such other functions as are assigned to him by the Chief Ombudsman.

## PART THREE
## *Rules Of Procedure Of The Institution*

22. *The Right to Lodge Complaints*

1) A complaint may be lodged by a person claiming to have suffered from maladministration or, by his spouse, family member, his representative or by a third aprty.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b75f9/

፪· እንደተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት ክብደት ተቋሙ የአመልካቹ ማንነት ሳይገለፅ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች ሊቀበል ይችላል።
፫· ማንኛውም ሰው ስለደረሰበት የአስተዳደር ጥፋት ለተቋሙ አቤቱታ ከማቅረቡ በፊት አግባብነት ላላቸው አካላት ደረጃውን ጠብቆ ቅሬታውን ማሰማት ይኖርበታል።
፬· በአንቀጽ ፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት በጉዳዩ የወንጀል ወይም የፍትሐ ብሔር ክስ መመስረትን አይከለክልም።
፭· ተቋሙ አቤታታዎችን ተቀብሎ የሚመረምረው ያለምንም ክፍያ ነው።

፳፫· ስለ አቤቱታ አቀራረብ
፩· አቤቱታ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ለተቋሙ ሊቀርብ ይችላል።
፪· አቤቱታዎች በተቻለ መጠን ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል።
፫· አቤቱታ እንደሁኔታው በአማርኛ ወይም በክልሉ የሥራ ቋንቋ ሊቀርብ ይችላል።

፳፬· ስለምርመራ
፩· ተቋሙ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ ምርመራ ሊያካሂድ ይችላል።
፪· ተቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ አነሳሽነት ምርመራ የማካሄድ ሥልጣን አለው።

፳፭· ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ስለማድረግ
ተቋሙ አስፈላጊ ማጣሪያዎችን ለማካሄድ በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ፣
፩· ተመርማሪዎች ለጥያቄ እንዲቀርቡ ወይም መልስ እንዲሰጡ፣
፪· ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ፣
፫· ለጉዳዩ ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ማስረጃ እንዲያቀርብ፣
ለማድረግ ይችላል።

፳፮· መፍትሔ ስለመስጠት
፩· ተቋሙ የቀረበለትን አቤቱታ በስምምነት ለመጨረስ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት።
፪· የምርመራውን ውጤት ከነአስተያየቱ ለሚመለከተው አካል የበላይ ኃላፊ እና ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሑፍ ያሳውቃል።
፫· ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚሰጠው አስተያየት ለተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት ምክንያት የሆነው ድርጊት ወይም አሠራር እንዲቆም ወይም ለጥፋቱ ምክንያት የሆነው መመሪያ ተፈጻሚነቱ ቀሪ እንዲሆንና የተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት እንዲታረም ወይም ተገቢ የሆነ ማንኛውም ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል።
፬· ለተቋሙ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

፳፯· ቅሬታ የማሰማት መብት
፩· ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ ወይም ተመርማሪ የተቋሙ የበታች ተሿሚ ወይም ኃላፊ በሰጠው የመፍትሔ ሃሳብ ቅሬታ ያለው ከሆነ የመፍትሔ ሀሳቡ በፅሑፍ ከደረሰው ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በደረጃው ቀጥሎ ለሚገኘው የተቋሙ ተሿሚ ወይም ኃላፊ ቅሬታውን የማሰማት መብት አለው።
፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቅሬታው የቀረበለት ተሿሚ ወይም ኃላፊ የተሰጠውን የመፍትሄ ሃሳብ ማሻሻል፣ ማገድ፣ መሻር ወይም ማፅናት ይችላል።
፫· በዋና ዕንባ ጠባቂው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፳፰· ጥፋት መፈጸሙን የማስታወቅ ግዴታ
ተቋሙ የምርመራ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ወንጀል መሠራቱን ያመነ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል ወይም ኃላፊ ወዲያውኑ በጽሑፍ የማስታወቅ ግዴታ አለበት።



2) The Institution may, in consideration of the gravity of the maladministration committed, receive anonymous complaints.
3) Prior to lodging a complaint with the Institution in respect of an act of maladministration from which he has suffered, any person shall bring the complaint before the relevant organs.
4) Without prejudice to the provisions of Article 7 hereof, the right to lodge complaints, as under this Proclamation shall be no bar to the institution of criminal or civil proceedings over the same case.
5) The Institution shall receive and investigate complaints free of any charge.

23. *Lodging Complaints*
1) A complaint may be lodged with the Institution orally, in writing, or in any other manner.
2) Complaints shall, to the extent possible, be submitted together with supporting evidence.
3) Complaints may be made in Amharic or in the working language of the Region.

24. *Investigation*
1) The Institution may conduct investigation on the basis of complaints submitted to it.
2) The Institution shall have the power to conduct investigation on its own initiation, where it so finds it necessary.

25. *Ordering the Production of Evidence*
In order to undertake necessary examination within a reasonable time, the Institution may order that:
1) those complained against appear for question or that they submit their defence;
2) witnesses appear, and give their testimony;
3) any person in possession of evidence relevant to the case, produce same.

26. *Remedies*
1) The Institution shall make all the effort it can summon to settle, a complaint brought before it amicably.
2) It shall notify, in writing, the findings of its investigation and its opinion thereon, to the superior head of the concerned organ and to the complainant.
3) The remedy proposed by the Institution, pursuant to Sub–Article (2) of this Article, shall expressly state that the act or practice having caused the maladministration be discontinued, or that the directive having caused same be rendered inapplicable, and that the maladministration committed be rectified, or that any other appropriate measure be taken.
4) Complaints submitted to the Institution shall be accorded due response, within a short period of time.

27. *The Right to Object*
1) Any complainant or accused shall have the right to object to the appointee or official next in hierarchy where he is aggrieved by a remedy proposed by a subordinate appointee, or official of the Institution, within one month from the time he is notified, in writing, of such proposed remedy.
2) An official who receives an objection, pursuant to Sub–Article (1) of this Article, may modify, stay the execution of, reverse or confirm the remedy having been proposed.
3) A decision rendered by the Chief Ombudsman shall be final.

28. *Duty to Notify a Fault*
Where the Institution, in the process of conducting investigations, believes that a crime or an administrative fault has been committed, it shall have the duty to, forthwith, notify in writing, immediately to the concerned organ or official.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

፳፱· ስለ ሥልጣን መደራረብ

፩· በተቋሙና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በማንኛቸው እንደሚመረመሩ በሁለቱ የጋራ ምክክር ይወሰናል።

፪· አንድን ጉዳይ የትኛው አካል እንደሚመረምር በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መወሰን ካልተቻለ አስቀድሞ የቀረበለት አካል ይመረምራል።

ምዕራፍ አራት

ስለተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔና

ስለተቋሙ ሠራተኞች አስተዳደር

፴· የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ

፩· የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔው እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡

ሀ) ዋና ዕንባ ጠባቂ .................................. ሰብሳቢ

ለ) ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ.................. ም/ሰብሳቢ

ሐ) ሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች ...................... አባላት።

፫· ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል።

፬· ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥነሥርዓት ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

፴፩· የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

ጉባዔው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡

፩· ይህን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል መመሪያዎችንና የውስጥ ደንቦችን ያጸድቃል፡

፪· በተቋሙ ረቂቅ በጀት ላይ ይመክራል።

፫· የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማ በመከተል የተቋሙ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ያጸድቃል፡

፬· መምሪያ ኃላፊዎችን ይሾማል፡

፭· የሚቀርቡለትን የሠራተኛ አስተዳደር ጉዳዮች ፡ ጥያቄዎች ወይም አቤቱታዎች መርምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል ፡

፮· የመምሪያ ኃላፊዎችን የዲሲፕሊን ጉዳዮች ያያል።

፴፪· ይግባኝ የማቅረብ መብት

፩· ጉባዔው በሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ቅር የተሰኘ የተቋሙ መምሪያ ኃላፊ ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፴፫· በሌሎች ባለሙያዎች ስለመገልገል

ተቋሙ ለተለየ ሥራና ለተወሰነ ጊዜ ተገቢ የሆነውን ክፍያ በመፈጸም ለሥራ የሚያስፈልጉትን የራሱ ያልሆኑ ባለሙያ ዎችን መድቦ ሊያሠራ ይችላል።

፴፬· ሚስጥር ስለመጠበቅ

በፍርድ ቤት ካልታዘዘ ወይም በዋናው ዕንባ ጠባቂ ካልተ ፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የተቋሙ ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ወይም በአንቀጽ ፴፫ መሠረት የተመደበ ባለሙያ በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን ምስጢር በማንኛውም ጊዜ የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

፴፭· ልዩ መብት

ማንኛውም የተቋሙ፡—

፩· ተሿሚ ከሆነ ምክር ቤቱ፤

፪· መርማሪ ከሆነ ዋና ዕንባ ጠባቂው፡

ሳይፈቅድ ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር አይያዝም፡ አይታሠርም።

29. *Overlap of Jurisdiction*

1) Where cases falling both under the jurisdiction of the Institution and of the Ethiopian Human Rights Commission materialize, the question of which of them would investigate shall be determined upon their mutual consultation.

2) Failing determination of the matter as under Sub-Article (1) of this Article, the organ before which the case is lodged shall undertake the investigation.

PART FOUR

*The Council of Ombudsmen and Administration of the Staff of the Institution*

30. *Council of Ombudsmen of the Institution*

1) Council of Ombudsmen of the Institution (hereinafter referred to as "the Council") is hereby established.

2) The Council shall have the following members:

(a) the Chief Ombudsman.................Chairperson

(b) the Deputy Chief Ombudsman.............Deputy

(c) other Ombudsmen ........................... Members.

3) The Council shall elect its secretary from among its members.

4) The Council may draw up its own rules of procedure.

31. *Powers and Duties of the Council*

The Council shall have the following powers and duties:

1) to adopt directives and by–laws necessary for the implementation of this Proclamation;

2) to discuss on draft budget of the Institution;

3) to adopt staff regulations in conformity with the basic principles of Federal Civil Service laws;

4) to appoint department heads;

5) to examine and render a final decision, within a short period of time, on cases, petitions or complaints submitted to it within short period of time in relation to staff administration;

6) to hear disciplinary cases relating to department heads.

32. *The Right to Appeal*

1) Any department head of the Institution aggrieved by administrative decisions rendered by the Council may appeal to the Speaker of the House within one month from the date such decision has been made.

2) Decisions rendered pursuant to Sub–Article (1) of this Article shall be final.

33. *Utilization of Outside Professionals*

The Institution may utilize, for a specific task and for a definite duration, outside professionals necessary for its functions, subject to making appropriate remunerations.

34. *Observance of Secrecy*

Unless ordered by a court or otherwise permitted by the Chief Ombudsman, any appointee, or staff, or Professional employed pursuant to Article 33 of this Proclamation shall have the obligation not to disclose, at all itmes, any secret known to him in connection with his duty.

35. *Immunity*

NO:

1) appointee, or

2) investigator

of the Institution may be detained or arrested without the permission of the House, or the Chief Ombudsman respectively, except when caught in *flagrante delicto*, for a serious offence.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

## ምዕራፍ አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፮· በጀት**

፩· የተቋሙ በጀት ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፣
   ሀ) በመንግሥት በሚመደብ በጀትና ድጎማ፣
   ለ) ከዕርዳታ፣ ከስጦታና ከማናቸውም ሌላ ምንጭ።

፪· ለተቋሙ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የየሦስት ወሩ ድርሻ የሆነ የሥራ ማስኬጃ በቅድሚያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ባንኩ በሚወክለው ሌላ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ በመንግሥት የፋይናንስ ሕግ መሠረት ለተቋሙ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ይውላል።

**፴፯· የሂሳብ መዛግብት**

፩· ተቋሙ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪· የተቋሙ ሂሳብ ምክር ቤቱ በሚሰይመው አካል በየዓመቱ ይመረመራል።

**፴፰· የመተባበር ግዴታ**

ተቋሙ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል።

**፴፱· መግለጫ ስለመስጠት**

፩· ተቋሙ እንደአስፈላጊነቱ ይፋዊ መግለጫ ይሰጣል።

፪· ተቋሙ መደበኛ ሪፖርቶች ማቅረብን ጨምሮ አሠራሩን በሙሉ ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል።

፫· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የአገሪቱ ጸጥታና ደኅንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ለማድረግ ወይም የግለሰቦችን የግል ሕይወት መብት ለመጠበቅ ሲባል በምስጢር ሊያዙ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ተቋሙ ጥንቃቄ የመውሰድ ግዴታ አለበት።

**፵· በስም ማጥፋት ስላለመጠየቅ**

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበ አቤቱታ በስም ማጥፋት አያስጠይቅም።

፪· ተቋሙ ስለሚያካሂደው ምርመራ ውጤት ምክር ቤቱ የሚያቀርበው ሪፖርት ወይም ሥራውን በማስመልከት የሚያደርገው ሌላ ዓይነት መጻጻፍ በስም ማጥፋት የሚያ ስጠይቅ አይሆንም።

**፵፩· ስለ ቅጣት**

፩· ማንኛውም ሰው በተቋሙ መጥሪያ ደርሶት ወይም በሌላ ሁኔታ ተጠርቶ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ወይም መልስ ካልሰጠ ወይም ሰነዶች ለማቅረብ ወይም ለማስመርመር ፈቃደኛ ካልሆነ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ሁለት መቶ እስከ ብር አንድ ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፪· በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ ምሥክሮች ሆነው በቀረቡ ወይም ሰነድ ባቀረቡ ሰዎች ላይ ጥቃት ካደረሰ ወይም በተቋሙ በቀረቡ ሪፖርቶች፣ በተሰጡት የማሻሻያ አስተያየቶችና ሀሳቦች ላይ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት እርምጃ ካልወሰደ ወይም እርምጃ የማይወስድበትን ምክንያት ካልገለጸ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ስድስት ሺ እስከ ብር አሥር ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

**፵፪· የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በምክር ቤቱ መታየት የተጀመሩ የአስተዳደር ጥፋቶችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች በተቋሙ ይታያሉ።



## PART FIVE
## *Miscellaneous Provisions*

36. *Budget*
   1) The budget of the Institution shall be drawn from the following sources:
      (a) budgetary subsidy to be allocated by the government;
      (b) assistance, grant and any other source.
   2) From the budget allocated to the Institution an amount equivalent to a quarterly portion of its recurrent budget shall, in advance, be deposited at the National Bank of Ethiopia, or at another bank designated by the Bank, and shall be utilized, in accordance with financial regulations of the government for purposes of implementing the objective of the Institution.

37. *Books of Accounts*
   1) The Institution shall keep complete and accurate books of accounts.
   2) The accounts of the Institution shall be audited annually, by an organ to be designated by the House.

38. *Duty to Cooperate*
   Any person shall provide the necessary assistance, with a view to helping the Institution exercise its powers and duties.

39. *Reporting*
   1) The Institution shall issue an official report, as may be necessary.
   2) The Institution shall exercise transparency in respect of its mode of operation, including issuance of regular reports.
   3) Notwithstanding the provisions of Sub–Article (2) of this Article, the Institution shall have the duty to exercise caution in respect of matters to be kept secret, with a veiw to not endangering national security and well–being or to protecting individual lives.

40. *Non–Answerability for Defamation*
   1) No complaint lodged pursuant to this Proclamation shall entail liability for defamation.
   2) No report of the Institution submitted to the House, on the findings of an investigation undertaken, nor any other correspondence of the Institution relating to its activities shall entail liability for defamation.

41. *Penalty*
   1) Any person who, having received summons from the Institution, or been called upon by it otherwise, does not appear or respond without good cause, within the time fixed, or is not willing to produce a document or to have same examined shall be punishable with imprisonment from one month to six months or with a fine from two hundered to one thousand Birr or with both.
   2) Unless punishable with more severe penalty under the penal law, any person who causes harm to persons who have witnessed before the Institution, or to persons having produced a document before it, or who, without good case, fails to take measures within three months from receipt of reports, recommendations, and suggestions of the Institution, or does not state the reasons for such failure, shall be punishable with imprisonment from three to five years or with a fine from six thousand to ten thousand Birr or with both;

42. *Transitory Provision*
   Complaints on maladministration that are under investigation by the House prior to the enactment of this Proclamation shall be investigated by the Institution.

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/

፵፫· ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፵፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፡ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

43. *Inapplicable Laws*

No law or practice, inconsistent with this Proclamation, shall be applicable in respect of matters provided for in this Proclamation.

44. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 4th day of July, 2000.

Done at Addis Ababa, this 4th day of July, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

PURL: https://www.legal-tools.org/doc/4b73f9/